



# "የአባይን ልጅ ውሃ ጠማው !"

የጐንቻው!

የሺ ዘመን እንቆቅልሽ የአበው ተረትና ምሳሌ፤
እነሆ ዛሬ ተፈታ ባዕድ፤ ባንዶች፤ የሸረቡብን ሴረኛ ውል እንደ 'ውጫሌ'፤
ተጋለጠ፤ የወያኔ የትውልድ የዘመናችን ደባ አባይን ሲሸጡ እንዳልባሌ፤
ሃያ ዓመት ተወይኖብን ስንጠላለፍ በእዚመኛ፤ ዘውገኛ ተከልለን በቀበሌ፤
መንደር እንጅ አገር የለን፤ ኢትዮጵያን የነጠቀን የነገር ሰው 'አፎሌ'፤
'ሕዳሴ' ብሎ አባይ ግድብ ትልቁ ሊጥ የተፈጨው፤ የተቦካው በአፈ - ጮሌ፤
በዲስኩር ራዕያቸው ሲያገምጡን የህልም አምባሻ 'ደግ - ሰው' ከመቀሌ፤
ጥሪት፤ሕይዎት እያስገበሩን ከጐጃም እስከ ወለጋ፤ ሸዋ፤ሀረር፤ አርሲ፤ከፋና፤ባሌ፤
ለካስ ቃል አባይ ኖረዋል፤ አፈር ቀማሹ ወደ ምድር 'የሰረጉት' ቀድመው በሃምሌ፤
ወንዛችንን እያቆሩ፤ ተስፋችንን የቀበሩ፤ ውሃ ያስጠሙን 'የኛ ጌቶች' የባዕድ ሎሌ፤
የኢትዮጵያን 'እህል-ውሃ' አስቀንነው ግብጽ፤ሱዳን ሊሲያስጋግሩ፤ካገር ሳይመክሩ ሸማግሌ፤
ዛሬ አረዱን! ኢትዮጵያ የአባይ ቋት እንጅ፤ አይደለችም እመቤት፤ባለቤት፤ የበኩር ልጁ ሾተሌ፤
መንታላ እናት አፈር ዱቄቷን የተቀማች፤ 'ጡት አጉርሳ' የነከሷት 'እማ-ወራ' ባተሌ፤
**ልጆቿን ውሃ ቢጠማቸው፤ አባይ ኩራዝ እንጂ ኮዳ አይሞላም ከጓዳቸው፤ካልፈረሰ ማነቂያ ውሉ እንደ 'ውጫሌ'።**

እናማ! የአባይ ልጅ ካሁን ወዲያ አባይ ላንተ የስለት ጠበል እንጂ ውሃ አይደለም፤
ከጊዮን የመነነ ስደተኛ አሮጌ አድባር ግብጽ የሻተው መንትዮሽ ካይሮ ሊያከትም፤
ጠላትና ገዥዎችህ ቆፈረው፤ ፈርመው የቀበሩት እንዳይፈስ በማሳህ በምድርህ ዳግም፤
ይብላኝ ላንተ፤ አባይ አንጀትህን፤አትብትህን፤አፈርህን እንጅ ራብ፤ጥምህን አይቆርጥም፤
አንጡራህን፤ ገመናህን ተራቁተህ በህዳሴ መዋጮ፤ በአገርህ፤ በተፈጥሮህ ላትጠቀም፤
ምን ብትማስን፤ መስኖ ላትተልም፤ ሺህ ብትቆፍር ጅረትህ በጓሮህ፤ በማሳህ አይወርድም፤
ከምድርህ ከርስ ቢሻቸው ቧንቧ አንጥፈው፤ አንጠፍጥፈው እንዲያስግሩት በሽልም፤
ሆድ ያዘዘበት ፓርላማ፤ አጨብጭቧል፤ ተፈራርሟል፤ ህሊና ቢስ፤ 'ምድረ ዳፍናታም'፤
**የአባይ ልጅ! አባይ ላንተ ስም እንጂ ፤ ከእንግዲህ ወዲያ ርሃብ ጥምህን አይቆርጥም።**

የአባይ ልጅ !፤ አንተንማ ማን ሰው ብሎህ፤ ሊያማክሩህ፤ ከመጤፍስ ሊቆጥሩህ፤

አይጎደል እንጂ ‘ወንዛቸው’ አንተንማ ‘አሳንሰው ያሰሉህ’ አሃዝ ሁነህ፤ በስድስት ዜሮ የቀነሱህ፤

ዛሬን እንጂ ‘ነገ አትኖርም’፤ ‘ተቆርጧልና’ በቀነኞች ‘ቀን እድርህ’፤

‘ግዑዝ ፓርላማ’ አጭብጮ የሸጠህ፤ የሸፈጠህ፤

ለፈርዖን ንጉሥ እጅ መንሻ ለዳርጎት ‘የቸረህ’፤

ዘመንህን፤ ለኅዳሴ፤ ቦንድ መግዣ ያጫረተህ፤

‘መንግሥትና ዘመን ወይነው ቢያራቁቱህ፤

ትሰደድ ይሆን የአባይን ፈለግ ተከትለህ?

‘በባቢሎን ከተማ የቀን ሥራው አማሎህ’

እርስትህን ትለቅ ይሆን ውለህ አድረህ?

የአባይ ልጅ እውን አንተን ውሃ ቢጠማህ፤

አታጎርፍም ወይ? በከተማህ፤ በመዲናህ፤

ቤተ-መንግሥት፤ውሃ ልኩን አጥለቅልቀህ፤

ዋናተኛው አትወጣም ወይ ከሥር ጠልቀህ፤

ዶሴ ፊርማውን ቀዳደህ፤ፈራሚውን አድፍቀህ፤

አንት የአባይ ልጅ! እንደ ጥንቱ ቃል ኪዳኑን አድሰህ፤

ልትነግር ለዓለም፤ ስለ ዓለም ብለህ፤

**አባይ ወንዛችን፤ መድህናችንም መሆኑን አስረግጠህ።**

yegonchaw@yahoo.co.uk 30.03.2015.

**<u>ማስታወሻነቱ</u>፡-**

አባይ ከብሄራዊ ስነ- ልቦናችን፤ ማንነታችን፤ ከታሪካችን፤ መልካ ምድራዊ አሰፋፈራችን፤ተፈጥሯዊ ትሥሥራችን ጋር ተቆራኝቶ ሺህ ዘመን አብሮን የነጐደ ከወንዝ የበለጠ ትርጉም፤ስላለውም እንደየዘመኑ የኑራችንን ፈተና ልንሻገርበት ምኞትና ሕልም ቋጥረን የምንፈታበት፤የእድገትና የልማታችንን ቁጭት የምንገልጽበት ሚስጥራዊ ኃይል መሆኑን የተረዱ የዘመኑ ገዥዎች በቀውጢው ሰዓት፤በፊታውራሪነት ከሚስጥር ኪሳቸው ሳይታሰብ ‘ህዳሴ ግድብ’ ብለው የመዘዙት ካርድ፤ነበርና አብዛኛውን ኢትዮጵያዊ ከኪስ ባለፈ፤በገዘፈ ብዙ፤ብዙ አስወጥቶታል።

በሌላ ወገን የቀነኞችን ታሪክና ምግባር የመረመሩ፤ ሌላ ድብቅ አጀንዳ ወይም ማዘናጊያ፤ከዚያም ቢያልፍ ብር መሰብሰቢያ እንጂ ብዙ ጥናት ሳይደረግ፤ ትርፍና ኪሳራው ሳይሰላ፤ ዓለም አቀፍ ብድርና እርዳታን ያላማከለ፤ሕግን በአግባቡ ያልተከተለ ‘የሕወኃት እድሜ ማራዘሚያ ክኒን’ ነው ብለው በጥብቅ ሲተቹት ቆይተዋል።

እነሆ ሰሞኑን የቀድሞው ፊታውራሪ አደራ ጠባቂና ጀሌዎቻቸው በድብቅ መክረውና አጥንተው ካርቱም የተመረቀ ‘የሶስትዮሽ ኃዳሴ ፊርማ’ ነጠላ ዜማ ለቀዋል፤ የግብጹ መሪም፤ ‘ፕረዚደንት አብድል ፋታህ ኢልሲሲ’ ድላቸውን በኛ ፓርላማ ተሰይመው ሲያነበንቡ ማጨብጨብ የለመደው ግብዝ፤ግ ዑዝ ‘የሕዝብ ተወካይ’ ተብዬ እስከታ መውረድ ብቻ ነበር የቀረው።

እናማ፤ወንዛችን አባይ እንገድበው፤እንጠጣው፤እናዘምረው፤የፈለግነውን የፈቀድነውን እንዲሆን፤ ከአምላክ ፈቃድና ችሮታ ጋር ሁሉም ኢትዮጵያዊ በሙሉ ነፃነት ይመክር፤ይዘክር፤ይወስንም ዘንድ እነዚህ ስንኞች ለሁላችን ማስታወሻ፤መታሰቢያም ይሁኑ፤፡